**የግብዓት ምርት ጥመርታ መወሰኛና ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ቁጥር - 1057/2017ዓ/ም እና የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገቡ ተጠቃሚዎች መመልመያ ረቂቅ መመሪያ ቁጥር - 1058/2017ዓ/ም መግለጫ**

## 1. መመሪያዎቹ የማሻሻል አስፈላጊነት፣

ቀደም ሲል የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ አዋጅ ቁጥር 768//2004 ለማስፈጸም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሁለት መመሪያዎች ወጥተው በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነርሱም መመሪያ ቁጥር 542/2013 የውጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768-2004 ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ እና መመሪያ ቁጥር 547/2013 አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ለመወሰንና ለማስፈጸም መመሪያ ናቸው፡፡ እነዚህ መመሪያዎች የተጠቀሰው አዋጅ መውጣት ተከትሎ የወጡ መመሪያዎች ሲሆኑ የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ማንኛውም ተቋም ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበረ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ማስመዝገብና ቁጥር ማሰጠት እንዳለበት አስገዳጅ ድንጋጌ መሠረት መመሪያዎቹ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግበው አሁን የያዙት የመመሪያ ቁጥር እንዲይዙ ተደርጓል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 768/2004 መውጣትን ተከትሎ እነዚህን ሁለት መመሪያዎች ማውጣት አስፈልጎ የነበረበት ምክንያት የመጀመሪያው በወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት መሠረት ለወጪ ምርት የሚሆን ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥ ነጻ በሚያስገቡት ወይም ጥሬ ዕቃው ከሀገር ውስጥ ከተጠቀሙ የቀረጥ ተመላሽ ተጠቃሚ የሆኑ ባለሃብቶች በሚያስገቡት ጥሬ ዕቃና ወደ ውጭ የሚልኩትን ምርት ለማምረት የተጠቀሙት የግብዓት መጠን ወጥነት የሌለውና የግብዓት ምርት ጥመርታውን ለማወቅ የሚያስችል አሠራርና መመሪያ ባለመኖሩ ጥሬ ዕቃዎቹ ከውጭ በሚገቡበትና በሚወራረዱበት ጊዜ ችግር ሲያጋጥም በመቆየቱ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በተጠቃሚዎች በየጊዜው ቀርበው ለመወሰን የሚታየውን ውጣ ውረድና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ወጪዎችን በመቀነስ ለወጪ ንግዱ የተቀላጠፈ አገልግሎትና አሠራር ማመቻቸት በማስፈለጉ ነው፡፡ ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ ለወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ፈጣን አገልግሎትና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ወጥ የሆነ አገር አቀፍ ስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ እነዚህ ሁለት መመሪያዎች ከአስር አመታት በላይ ሲሰራባቸው ቆይተዋል፡፡ ከእነዚህ የሥራ አመታት በኋላ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዋጁ የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶችን በተዋጣ መልኩ ለማስፈጸም የተጠቀሱት መመሪያዎች መሻሻል ያለባቸው ስለመሆኑ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ የደረሰበት ድምዳሜ ነው፡፡ መሥሪያ ቤቱን ከዚህ ድምዳሜ ላይ ያደረሰው እና የተጠቀሱት መመሪያዎች የማሻሻል አስፈላጊነት ገፊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- ✓ በዘርፉ እያደገ የመጣውን ፍላጎት በሚፈለገዉ ደረጃ ለማርካት እና በቀጣይ ከዘርፉ የሚጠበቀውን የወጭ ንግድ ግብን ለማሳካት የሚያስችሉ ድጋፎችን ለዘርፉ ኢንዱስትሪዎች ለማቅረብ፣
- ✓ ተዘጋጅተው ተግባራዊ የተደረጉ የማበረታቻ ማዕቀፎችን እና የአሰራር ስርዓቶችን አፈጻጸም በመገምገም የአሰራር ስርዓት ማስተካከያ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣
- ✓ በተለያዩ ጊዜ የወጡ መመሪያዎች ለሁሉም ዘርፎች በሚያሰራ መልኩ ወደ አንድ በማምጣት ተደራሽ እንዲሆኑና የተናበቡ እንዲሆኑ ለማድረግ፣
- ✓ በሀገራችን እየሰፋ የመጣውን ኢንዱስትሪ ዕድገት ሊደግፍ በሚያስችል መልኩ ወቅታዊ ለማድረግ፤
- ✓ ፈጣን አገልግሎትና ውሳኔ ለመስጠት እንዲቻል

ነው፡፡

## 2. የረቂቅ መመሪያዎቹ ይዘት፣

### 2.1. <u>የግብዓት ምርት ጥመርታ መወሰኛና ማስፈጸሚያ ረቂቅ መመሪያ ይዘት</u>

ክፍል አንድ- ጠቅላላ

- ✓ አጭር ርዕስ
- ✓ ትርጓሜ

ክፍል ሁለት- የግብዓት ምርት ጥመርታ የሚያዘጋጁ አካላት ማቋቋም እና ተግባራት

- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ የሚያዘጋጁ አካላትን ስለማቋቋም እና ስለመሰየም
- ✓ የዓብይ ኮሚቴ አወቃቀር

- ✓ የዓብይ ኮሚቴ ተግባራት
- ✓ የዓብይ ኮሚቴው የስብሰባ ጊዜ እና የውሳኔ አሰጣጥ
- ✓ የቴክኒክ ኮሚቴን ስለመሰየም
- ✓ የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባራት
- ✓ የመሪ ሥራ አስፈጻሚ ተግባራት

ክፍል ሦስት- የግብዓት ምርት ጥመርታ ዝግጅት፣ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚገባበት አግባብ እና የተጠቃሚዎች የጥያቄ አቀራረብ

- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ ዝግጅት
- ✓ የምርት ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት
- ✓ የተጠቃሚዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ጥያቄ አቀራረብ

ክፍል አራት- የግብዓት ምርት ጥመርታ ይዘት፣ አወሳሰን እና አተገባበር

- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ ይዘት
- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ መለኪያ አወሳሰን
- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ የፍጆታ መጠን አወሳሰን
- ✓ በምርት ሂደት ስለሚባክን የግብዓት መጠን አወሳሰን፣
- ✓ የባከነ ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ገበያ እንዲሸጡ አወሳሰን
- ✓ በምርት ሂደት ጉድለት የተገኘባቸው ምርቶች አወሳሰን
- ✓ በምርት ሂደት ጉድለት የተገኘባቸው ምርቶች መጠን አወሳሰን እና በሀገር ውስጥ እንዲሸጡ ስለመፍቀድ
- ✓ በሌሎች ምክንያቶች ምርቶች በሀገር ውስጥ እንዲሸጡ ስለመፍቀድ
- ✓ የተመሳሳይ ስያሜ ወይም ተተካኪ የግብዓት ምርት ጥመርታ አወሳሰን

- ✓ ስለማሸጊያ ወይም መጠቅለያ እና አላቂ የምርት መገልገያዎች አወሳሰን
- ✓ የምርት ግብዓቶች ተመሳሳያቸው በሀገር ውስጥ የማይገኙ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት
- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ የማጽደቂያ የጊዜ ገደብ
- ✓ የግብዓት ምርት ጥመርታ ያልተዘጋጀላቸው የምርት ምድቦች
- ✓ የግብዓት ምርት  ጥምርታ አተገባበር

ክፍል አምስት- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

- ✓ የቅሬታ አቀራረብ
- ✓ መሸጋገሪያ ድንጋጌ
- ✓ ስለአባሪዎችና ቅጾች
- ✓ የተሻሩ መመሪያዎች እና አሠራሮች
- ✓ መመሪያውን ስለማሻሻል
- ✓ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

## 2.2. <u>የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገቡ ተጠቃሚዎች መመልመያ ረቂቅ መመሪያ ይዘት</u>

ክፍል አንድ- ጠቅላላ

- ✓ አጭር  ርዕስ
- ✓ ትርጓሜ
- ✓ የተፈጻሚነት ወሰን

ክፍል ሁለት- የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

- ✓ የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ለሚኒስቴሩ ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤
- ✓ የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

- ✓ በዱቤ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ጥሬ ዕቃን ወደ ሀገር ያስገባ አመልካች የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወቀረት ለማግኘት መሟላት ስላለበት ቅድመ ሁኔታዎች፣

ክፍል ሦስት- የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

- ✓ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤
- ✓ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

ክፍል አራት- የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ስለማግኘት

- ✓ የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤
- ✓ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

ክፍል አምስት- የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ስለማግኘት

- ✓ የቦንድድ ግባዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከት የሚችሉ ሰዎች፤
- ✓ የቦንድድ ግባዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

ክፍል ስድስት- የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ ስለመመልመል

- ✓ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ የመመልመያ መስፈርት
- ✓ የመመልመያ ነጥብ አሰጣጥ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት
- ✓ ማመልከቻ ስለማቅረብ

ክፍል ሰባት- ስለምስክር ወረቀት ሰጪው አካል ተግባራት እና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

- ✓ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ኃላፊነት
- ✓ የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ተግባራት
- ✓ በተጠቃሚዎች የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ትክክለኛነትን ስለማረጋገጥ

- ✓ የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ
- ✓ የምስክር ወረቀት ይዘት
- ✓ የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ጊዜ
- ✓ የምስክር ወረቀት  ስለማደስ
- ✓ የምስክር ወረቀት ስለሚታገድበት ሁኔታ
- ✓ የምስክር ወረቀት ስለሚሰረዝበትና በድጋሚ ስለሚወሰድበት ሁኔታ

ክፍል ስምንት- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

- ✓ የአገልግሎት ክፍያ
- ✓ ቅሬታ ስለማቅረብ
- ✓ የምስክር ወረቀት ስለማደስ
- ✓ የምስክር ወረቀት ስለሚታገድበት ሁኔታ
- ✓ የምስክር ወረቀት ስለሚሰረዝበትና በድጋሚ ስለሚወሰድበት ሁኔታ
- ✓ መሸጋገሪያ ድንጋጌ
- ✓ የተሻሩ መመሪያዎች
- ✓ መመሪያውን ስለማሻሻል
- ✓ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

3. **በረቂቅ መመሪያዎቹ ዝግጅት የተሳተፉ አካላት፣**

- የኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት፣
- ጉዳዩ የሚመለከታቸው በፌደራል ደረጃ የሚገኙ መሥሪያ ቤቶች፤
    - የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ስር የሚገኙ የማዕከላት፣
    - የግብርና ሚኒስቴር
    - የገቢዎች ሚኒስቴር ፣
    - የጉምሩክ ኮሚሽን እና
    - የኢንቨስትመንት ኮሚሽን፡፡

## 4. በረቂቅ መመሪያዎቹ ላይ የተደረጉ ውይይቶች፣

### 4.1. ከየምርት ምድቡ አምራቾች ጋር የተካሄደ የግብአት ማሰባሰቢያ ውይይት፤

- ✓ ግንቦት 12 ቀን ቀን 2016ዓ.ም ምግብና መጠጥ አምራቾች ጋር በምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከል የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣
- ✓ ግንቦት 14 ቀን ቀን 2016ዓ.ም የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ አምራቾች ጋር በአዝመን ሆቴል፣
- ✓ ግንቦት 15 ቀን ቀን 2016ዓ.ም ኬሚካል እና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አምራቾች ጋር በካሌብ ሆቴል፣
- ✓ ግንቦት 16 ቀን ቀን 2016ዓ.ም ቆዳና የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ጋር በካይዘን ማዕከል፣
- ✓ ግንቦት 20 ቀን 2016ዓ.ም የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾች ጋር በሐዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ እና
- ✓ ግንቦት 21 ቀን 2016ዓ.ም ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አምራቾች ጋር በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣
- ✓ ግንቦት 27 ቀን ቀን 2016ዓ.ም ሆርቲካልቸርና አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች በካፒታል ሆቴል፡፡

### 4.2. ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላትጋር የተካሄደ የግብአት ማሰባሰቢያ ውይይት፤

ሐምሌ 2 ቀን 2016ዓ.ም ደብረ ዘይት ቲኬ ሆቴል እና ነሐሴ 22 ቀን 2016ዓ.ም በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መሰብሰቢያ አዳራሽ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ ባለድርሻ አካላት ጥሪ ተደርጎ ከገንዘብ ሚኒስቴር በቀር የተቀሩት ጥሪ የተደረገላቸው አካላት ማለትም የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት በረቂቅ መመሪያዎቹ ላይ የውይይት ተካሄዷል፡፡

### 4.3. አስተያት ለመቀበል የተላለፈ የማስታወቂያ ጥሪ፣

ረቂቅ መመሪያዎቹ ተደራሽ ለማድረግ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድረገ ገጽ ላይ እንዲለጠፍ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በመቀጠልም በረቂቅ መመሪያዎቹ ላይ አስተያየት ያለው ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም ረቂቅ መመሪያዎቹን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድረ ገጽ በማውረድ ወይም በአካል መጥቶ የመመሪያዎቹን ኮፒ በመውሰድ ያለውን አስተያት በአካል ማቅረብ ወይም በኢሜል አድራሻ legalservice.moi@gmail.com እንዲልክ ግንቦት 25 ቀን 2016ዓ.ም

በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ሁለት ግለሰቦች አስተያታቸውን ሰጥተዋል፡፡

## 5. ማሻሻያ የተደረገባቸው ነጥቦች፣

### 5.1 <u>መመሪያ ቁጥር 547/2013 ላይ ማሻሻያ የተደረገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች</u>

1) **ርዕስ**

ይህ መመሪያ ለአንድ የወጪ ምርት የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች መወሰን ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በቀድሞው መመሪያ ርዕስ ውስጥ ‹‹አገር አቀፍ ስታንዳርድ ›› የሚለው ቃል የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ከሚያዘጋጀው ስታንዳርድ ጋር ግንኙነት ያለው እንዳያስመስል በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 1)

2) **የተፈጻሚነት ወሰን**

- በአዋጁ ከተገለጹት ስድስት የማበረታቻ ሥርዓቶች ውስጥ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መመሪያ እንዲያወጣና እንዲያስፈጽም ሥልጣን የተሰጠው የአምስቱ የማበረታቻ ሥርዓቶች ማለትም የቫውቸር ሥርዓት፤ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት፤ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት፤ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት እና ኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ናቸው፡፡ (አንቀጽ 3)
- በነባሩ መመሪያ በአዋጅ ቁጥር 768/2004 ውጪ በሌሎች ሕጎች ለተጠቀሱ ማበረታቻዎችም መመሪያው ተፈጻሚ እንዲሆን በሚያመለክት መልኩ በድንጋጌው የተጠቀሰው ከማሻሻ ረቂቅ መመሪያው እንዳይካተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 3)

3) **የግብዓት ምርት ጥመርታ የሚያዘጋጁ አካላትን ስለማቋቋም እና ስለመሰየም**

- በነባሩ መመሪያ የግብዓት ምርት ጥመርታ ዝግጅት በኮሚቴ እና በቴክኒክ ኮሚቴ እንደሚከናወን ከመግለጽ ውጪ በማን እንደሚሰየሙ የሚያመለክት ድንጋጌ አላካተተም፡፡(አንቀጽ 4)
- በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው የግብዓት ምርት ጥመርታን የሚያዘጋጁ አካላት እነማን እንደሆኑ፣ በማን እንደሚሰየሙ ፣ ተጠሪነታቸው ለማን እንደሆነ እና የእያንዳንዱ አካላት ተግባራት ምን ምን እንደሆነ ለማመልከት በክፍል ሁለት ሰባት አንቀጾችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚሁ መሠረት አንቀጽ 4 ሚኒስቴሩ እነዚህን አካላት እንደሚሰይም በግልጽ ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ 4)

- በነባሩ መመሪያ የአበይት ኮሚቴው አወቃቀር የተመለከተ ድንጋጌ አልያዘም፡፡ ይህ ኮሚቴ ቁጥሩ ምን ያህል መሆን እንዳለበት፣ ከየት መንግሥታዊ መሥታዊ ተቋማት የተውጣጡ መሆን እንዳለበት እና ተጠሪነቱ ለማን እንደሆነ የሚያመለክት ድንጋጌ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲካተት ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 5)
- በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው የዓበይት ኮሚቴው የግንኙነትና የስብሰባ ጊዜ ወጥ እንዲሆን ወስኖ አስቀምጧል፡፡ ይህ ድንጋጌ በነባሩ መመሪያ ውስጥ ያልነበረ በመሆኑ የተነሳ ኮሚቴው በመደበኛነት እንዲገናኝ እና ተግባራቱን በወቅቱ እንዳይፈጽም እና የጉዳዮች መጓተትን አስከትሎ ቆይቷል፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ይህን አዲስ ድንጋጌ ማካተት ያስፈለገው የተጠቀሰውን የመዘግየት ችግር ለመፍታት እንዲረዳ ነው፡፡ (አንቀጽ 7)
- ለእያንዳንዱ የምርት ምድብ የሚሰየሙት የቴክኒክ ኮሚቴዎች እንደማን እንደሆኑ እና ከየትኛው ተቋም እንደሆኑ አያመለክትም፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ግን እንደማን እንደሆኑ፣ ከየትኛው ተቋም እንደሚሰየሙ እና በቀጣይም አዲስ ለሚመጡ የምርት ምድቦች የቴክኒክ ኮሚቴ እንዴት ሊሰየም እንደሚችል ጭምር የሚያመለክት አዲስ ድንጋጌ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 8)
- በነባሩ መመሪያ መሠረት ማንኛውም ከግብዓት ምርት ጥመርታ ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ተግባራትን የማስተባበር ሥራ እየሰራ የሚገኘው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የማበረታቻና ማስፋፊያ መሪ የሥራ አስፈጻሚ (የሥራ ክፍል) ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የሥራ ክፍል የሚፈጽመው ተግባራት እና ያለበት ኃላፊነት ዝርዝር በነባሩ መመሪያ አልተካተተም፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ውስጥ ይህ የሥራ ክፍል ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት ዝርዝር እንዲካተት እና የሕግ መሠረት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 10)

## 4) የግብዓት ምርት ጥመርታ ዝግጅት

- በነባሩ መመሪያ የብክነት መጠንን የተመለከተ ድንጋጌ አላካተተም፡፡ ነገር ግን ለየምርት ምድቡ ከተዘጋጁት አባሪዎች (ማጣቀሻዎች) መካከል የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት አባሪ (የምርት መለያ B) ብክነት ታሳቢ እንደሚደረግ ደንግጓል፡፡ የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው የብክነት ጉዳይ ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ውጭ ሌሎች የምርት ምድቦችንም የሚመለከት መሆኑን በመውሰድ ይህንኑ እንዲያካተት ተደርጎ ተካቷል፡፡ (አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3)

- በነባሩ መመሪያ ለወጪ ምርት የሚያገለግሉ አላቂ ምርት መገልገያዎች ፣ ማሽኒያና መጠቅለያ ግብዓት ምርት ጥመርታ እንደሚዘጋጅላቸው በግልጽ ያመለከተ ስላልነበረ እና አላቂ ምርት መገልገያዎች ፣ ማሽኒያና መጠቅለያ ግብዓቶች ለሌሎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርት ስለሆነ በዚሁ አግባብ ግብዓት ምርት ጥመርታ የሚዘጋጅላቸው መሆኑን የሚያመለክት አዲስ ድንጋጌ ተጨምሯል፡፡ (አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4)
- ወጥ የሆነ የፍጆታ ስሌትን በነባሩ መመሪያ ያልነበረ ሲሆን በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው የፍጆታ ስሌትን ከማዕከል ማዕከል እንዲሁም በሚመለከተው ተቋም ወጥነተ እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል አዲስ ድንጋጌ እንዲተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 5)
- በነባሩ መመሪያ የወጪ ምርት ወይም ግብዓት ለአንድ ድርጅት ብቻ/ Company Standard/ Brand Rate የሚሆን የግብዓት ምርት ጥመርታ ማዘጋጀት እንዲቻል ፈቃጅ የሆነ ድንጋጌ አላካተተም፡፡ ነገር ግን ይህን መሰል ጉዳይ ሲገጥም ሙሉ ለሙሉ እንዳይሰተናገድ ከማድረግ ይልቅ እንደጉዳዩ አግባብነት እየታየ ሊስተናገድ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ እንዲኖር ለማስቻል በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ውስጥ በግልጽ እንዲካተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 7)

5) **የተጠቃሚዎች የግብዓት ምርት ጥመርታ ጥያቄ አቀራረብ**

- የሥርዓቱ ተጠቃሚ የግብዓት ምርት ጥመርታ የይጽደቅልኝ ጥያቄ ለማቅረብ በቅድሚያ በጸደቀው የግብዓት ምርት ጥመርታ ውስጥ ያልተካተተ እና በየትኛው ኮድ መስተናገድ እንደሚችል በነባሩ መመሪያ ያልነበረ በመሆኑ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲካከተት ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 7)
- በነባሩ መመሪያ ላይ  የስርዓቱ ተጠቃሚዎች መቸ ጥያቄ ማቅረብ እንዳለባቸው በግልጽ ያልተቀመጠ በመሆኑ ተጠቃሚዎች የማወራረጃ ጊዜያቸው ሊያልቅ ጥቂት ቀናት ሲቀራቸው የአዲስ ጥምርታ ይጽድቅልኝ ወይም የይሻሻልልኝ ጥያቄ እያቀረቡ የማወራረድ ሥራዉ ከአንድ አመት ባላይ እንዲወስድ እያደረገው ስለሆነ ይህን ለመቅረፍ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ማካተት አስፈልጓል፡፡ (አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 3)
- የፍጆታ ልዩነቱ ከ5 በመቶ በታች ከሆነ በጸደቀው ጥምርታ እንዲስተናገድ እና ሌላ ጥምርታ ማዘጋጀት የማያስፈልግ በመሆኑ (አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4)
- የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው አስፈላጊነት አንዱ ለባለጉዳዮች የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት በመሆኑ እንደዚሁም የተተካኪ ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ሙያዊ እይታ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን የተተካኪን ጥያቄ በቀጥታ በማዕከላት

ወይም በሚመለከተው ተቋም ምላሽ እንዲያገኝ በሚያስችል አግባብ ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4)

6) **የግብዓት ምርት ጥመርታ ይዘት**

- ለሁሉም የምርት ምድቦች የሚዘጋጁ እና በሚኒስትሩ የሚጸድቁ የግብዓት ምርት ጥመርታ ሰነዶች ወጥነት እንዲኖራቸው ለማስቻል ይዘታቸው ምን ምንን ማካተት እንዳለበት አስገዳጅ ድንጋጌ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ማካተት በማስፈለጉ ነው፡፡ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ 14)

7) **በምርት ሂደት ስለሚባክን የግብዓት መጠን አወሳሰን**

- በምርት ሂደት የሚባክን ግብዓት በግብዓት ምርት ጥመርታ ውስጥ ታሳቢ የሚደረግ ሆኖ መጠኑን በመወሰን ላይ በውሳኔ ሰጪው ፍላጎት እንዳይቀየር ሲባል ውሳኔው በግብዓት ምርት ጥመርታ ወይም አባሪው ላይ በተጠቀሰው አግባብ እንዲሆን መርህ ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን በግብዓት ምርት ጥመርታው ከተቀመጠው መጠን በላይ የሆነ ጉዳይ ሲገጥም በልዩ ሁኔታ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲካተት ተደርጓል፡፡ የብክነት መጠንን መወሰን የምርት ምድቡ የሙያ ጉዳይ ብቻ ባለመሆኑ በልዩ ሁኔታ ውሳኔ ለመወሰን ጥንቃቄ እንዲኖር ለማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ በሚኒስትሩ መወሰን እንዳለበት በማመልከት ተደንግጓል፡፡ (አንቀጽ17 ንዑስ አንቀጽ 1 ፣ 2፣3 እና 4)

8) **ጉድለት ስለተገኘበት ምርት፣**

- አንድ የወጪ ምርት በማምረት ሂደት ጉድለት የተገኘበት ወይም ወደ ውጭ ተልኮ በጉድለት ምክንያት ተመላሽ ሲደረግ በእርግጥ ምርቱ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ፣ ስለጉድለቱ መጠን አወሳሰን እና በሀገር ውስጥ እንዲሸጥ ስለሚወሰንበት አግባብ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲካተት ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 19 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3)

- ነገር ግን ምርቱ ጉድለት ሳይኖርበት እና የኤክስፖርት ደረጃውን ጠብቆ ተመርቶ ሲያበቃ ወደ ውጭ መላክ የማይቻልባቸው ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ ይህን መሠሉ ሁኔታ ኮቪድ 19 በተከሰተበት ወቅት ምርቶች ወደ ውጭ መላክ ያልተቻለበት፣ መላክ ቢቻልም ገዢዎች ከጤና ስጋት በመነጨ አንረከብም ያሉበት ሁኔታ በገሃድ ታየወቷል፡፡ በመሆኑም ጉድለትን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ሲገጥሙ የወጪ ምርቶች ሀገር ውስጥ እንዲሸጡ ስለሚፈቀድበት አግባብ በመመሪያው እንዲካተት ተደርጓል፡፡ (አንቀጽ 21)

9) **የተመሳሳይ ስያሜ ወይም ተተካኪ የግብዓት ምርት ጥመርታ አወሳሰን**

- የተመሳሳይ ወይም የተተካኪ የግብዓት ጉዳይ በተግባር የገጠመና በአሰራር ደረጃ የነበረውን ግልጽ የሆነ የሕግ መሠረት እንዲኖረው ለማስቻል ሲባል በዚህ የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ እንዲካተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ )

10) **የምርት ግብዓቶች ተመሳሳያቸው በሀገር ውስጥ የማይገኙ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት**

- ማንኛውም ግብዓት ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በጥራት ተመሳሳዩ ሀገር ውስጥ የማይገኝ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የማረጋገጥ ኃላፊነት ግዴታ አለበት፡፡ ይህ በአዋጁ አንቀጽ 28 ተመላክቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ቅድመ ሁኔታ ተግባራዊ ሲደረግ አልነበረም፡፡ ይህ አለመደረጉ በተለይ የሀገር ውስጥ አምራቹን ሊጎዳ የሚችልበት ዕድል ሊፈጥር ስለሚችል በአዋጁ የተቀመጠውን አጠቃላይ አነጋገር ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል ዝርዝር ድንጋጌዎች በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ እንዲካተት ተደርገዋል፡፡ (አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 3)
- ሆኖም ግን ይህን ጉዳይ በነባሩ መመሪያ ማለትም መመሪያ ቁጥር 547/2013 ላይ ባይገለጽም በመመሪያ ቁጥር 542/2013 አንቀጽ 18 ተገልጧል፡፡ ነገር ግን የተገለጸበት አግባብ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማንኛውም ግብዓት ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ከመፍቀዱ በፊት በጥራት ተመሳሳዩ ሀገር ውስጥ ስለመኖር አለመኖሩ እንደቅድመ ሁኔታ ይዞ የማጣራት ግዴታ እንዳለበት ሳይሆን ሚኒስቴሩ በፈለገ ጊዜ የሚፈጽመው ጉዳይ እንደሆነ በተጨማሪም በዚህ ገደብ እጠቀማለሁ የሚል ሰው ግብዓቱ በሀገር ውስጥ መኖሩን ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ በመጣል ነው በመመሪያው የተገለጸው፡፡ ነገር ግን ይህ በአዋጁ ከተደነገገው ያፈነገጠ ነው (አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 3)

11) **የግብዓት ምርት ጥመርታ የማጽደቂያ የጊዜ ገደብ**

- ነባሩ መመሪያ መሻሻል እንዳለበት ከተነሱ ምክንያቶች አንዱ በመመሪያ አፈጻጸም ላይ የሚሳተፉ አካላት ፈጣን ውሳኔ አለመስጠታቸውን የተመለከተ ነው፡፡ እነዚህ አካላት ውሳኔያቸውን የሚሰጡበት የጊዜ ገደብ አልተቀመጠም፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ የቴክኒክ ኮሚቴዎች፣ ዐብይ ኮሚቴው እና ሚኒስቴሩ ውሳኔ የሚሰጡበት የጊዜ ገደብ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4)

12) **የግብዓት ምርት ጥመርታ ያልተዘጋጀላቸው የምርት ምድቦች**

- በአብዛኛው በዚህ መመሪያ የሚስተናገዱት ግብዓቶች በዚህ መመሪያ መሠረት የግብዓት ምርት ጥመርታ የተዘጋጀላቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን ለወጪ ምርት የሚሆን ግብዓት ቀርቦ ነገር ግን የግብዓት ምርት ጥመርታ ያልተዘጋጀለት በሚሆንበት ወቅት ባለጉዳዩን ወይም ተጠቃሚውን አላስተናግድም ብሎ ከመመለስ ይልቅ ጉዳዩ እንደአስፈላጊነቱ እየተመረመረ እንዲስተናገድ የሚደረግበት አግባብ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዲካተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 26)

13) **የቅሬታ አቀራረብ**

- ከነባሩ መመሪያው አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ቅሬታ ያለው ባለጉዳይ ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ወገን ቅሬታውን በምን አግባብ ማቅረብ እንዳለበት የሚያመለክት ድንጋጌ አልያዘም፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ ጉዳዮች በመመሪያ በተቀመጡ የጊዜ ገደብ እንዲፈጸሙ በማድረግ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲያገኙ ለመደገፍ፣ መመሪያውን በማስፈጸሚ ሂደት የሚተሳፉ የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ከመመሪያው ውጪ ለሚፈጽሙት ያልተገባ አድራጎት ተጠያቂነትና ኃላፊነታቸው እንዲኖርባቸው ለማስቻል ባለጉዳዮች ቅሬታቸውን የሚያቀርቡበት አግባብ የሚያመለክት ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 28)

14) **ስለአባሪዎችና**

- በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው መሠረት በመርህ ደረጃ ለሁሉም የምርት ምድቦች የግብዓት ምርት ጥመርታ የሚዘጋጀው በመመሪያው ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ ይህ በሁሉም የምርት ምድቦች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የመመሪያው ገዢ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከየምርት ምድቡ ባህሪይ አኳያ ሙያዊ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዙ ለእያንዳንዱ የምርት ምድብ የሚያገለግሉ አባሪዎች ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘዋል፡፡ እነዚህ አባሪዎች የመመሪያው አካል እንደሆኑ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የመመሪያው አካል እንደመሆናቸው መጠን በቀጣይ አባሪዎች ሲሻሻሉ መመሪያው እንደተሸሻለ ስለሚቆጠር መመሪያ በሚሻሻልበት አግባብ እንዲሻሻሉ ያስገድዳል፡፡(አንቀጽ 30)

## 5.2 መመሪያ ቁጥር 542/2013 ላይ ማሻሻያ የተደረገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች

1) ርዕስ

- ነባሩ መመሪያ ከምስክር ወረቀት አሰጣጥ በተጨማሪ በአዋጁ ሥልጣኑ የገንዘብ ሚኒስቴር የሆነውን በአንቀጽ 6 እና 7 ላይ ስለተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት የተመለከተውን እንደዚሁም ከምስክር ወረቀት አሰጣጥ ጋር ያልተያያዙ በአንቀጽ 14 ጥሬ ዕቃ ወይም በጥሬ እቃው የተመረተው ምርት ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ስለሚተላለፍበት ሁኔታ፣ በአንቀጽ 15 ስለብክነትና ብልሽት መጠን፣ በአንቀጽ 18 ተመሳሳያቸው አገር ውስጥ ስለሚመረቱ ግብዓቶች እና በአንቀጽ 19 ስለአገር አቀፍ የግብዓት ምርት ጥመርታ ይዟል፡፡ ( አንቀጽ 1 )
- የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ትኩረት ያደረገው የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ላይ ብቻ በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትና በነባሩ መመሪያ ውስጥ የነበሩት ድንጋጌዎች ከማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የማሻሻያ ረቂቅ የመመሪያው  በምስክር ወረቀት አሰጣጥ ላይ የተወሰነ በመሆኑ ይህንኑ በሚገልጽ  መልኩ " <u>የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ</u> " የሚል ርዕስ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡( አንቀጽ 1 )

2) የቫውቸር ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፤

- የአዋጁ አንቀጽ 8 እንደሚያመለክተው የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሕጉ የፈቀደላቸው አምራች ላኪዎች፣ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች እና ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ብቻ ናቸው፡፡፡ ነገር ግን በቀድሞው መመሪያ ቀጥተኛ ያልሆኑ ላኪዎችና ላኪዎች የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች እንደሆኑ ተደርጎ ተካተዋል፡፡ ሌላው በዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆን በአዋጁ አንቀጽ 8 ላይ የተጠቀሰው ጥሬ ዕቃ አቅራቢ በነባሩ መመሪያ ሳይካተት ቀርቷል፡፡ የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ይህን በማረም እና የአዋጁን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች  አምራች ላኪዎች፤ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፤ እና ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ብቻ መሆናቸው በማመልከት ተደንግጓል፡፡(አንቀጽ 4)
- የምስክር ወረቀት ጠያቂው የሂሳብ መግለጫ(አንቀጽ 8(ሠ)  እና  ተረፈ ምርት (አንቀጽ 8(ተ) በነባሩ መመሪያ የነበሩ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሆኑ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ ውስጥ እነዚህ ነጥቦች እንደቅድመ ሁኔታ እንዳይወሰዱ ወይም እንዳይካተቱ ተደርጓል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ነባሩን መመሪያ ለማሻሻል መነሻ ከሆኑ ምክንያቶች አንዱ ለተጠቃሚዎች ቀልጣፋ

አገልግሎት ለመስጠት ሲሆን ይህንን እሳቤ እንዲሳካ ለመደገፍ ወሳኝ ያልሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲቀነሱ ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 5)

3) **የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፤**

- በነባሩ መመሪያ የሂሳብ መግለጫ(ንዑስ አንቀጽ 5)፣ የድርጅቱ አጠቃላይ መግለጫ(ንዑስ አንቀጽ 6)፣ የጥሬ ዕቃዎች ዝርዝር ማቅረብ(ንዑስ አንቀጽ 8) እና የግብዓት አጠቃቀም ለውጥ ካለ የግብዓት ምርት ጥመርታ ማጸደቅ(ንዑስ አንቀጽ 9) የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያ እናዳይካተት ተደርጓል፡፡ ይህ አማራጭ የተወሰደበት ምክንያት ከላይ ለቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ለማሻሻል እንደ ተገለጸው ሁሉ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚዎችም ቅድመ ሁኔታዎችን ለመቀነስ እና ቀላጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል ለማድርግ ነው፡፡ (አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 9)

4) **የቦንድድ ግባዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፤**

- በአቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን በነባሩ መመሪያ ተካተው ከነበሩት መስፈርቶች መሐከል አመልካቹ የውጭ ድርጅት ከሆነ በራሱ ድርጅት እያመረተ የሚገኝ መሆን፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ማቅረብ የሚችሉና ለዚህም በቂ ክምችት የሚይዝ መሆኑን፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግር የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ለመስጠት ፍቃደኛ የሆኑ እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ጥሬ ዕቃዎችን ከአገር አስወጥተው ለማስወገድ የሚችሉ መሆኑን፣ በአገር ውስጥ ለማምረት ፍላጎት ያላቸው እና ይህንንም በቀጣይ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ መተግበር የሚጀምሩ መሆኑን፣አቅራቢዎቹ ኬሚካልና ዳይስታፍ የሚያቀርቡ ከሆነ ዕውቅና ካለው ላቦራቶሪ የየኬሚካሎቹን የፍተሻ ውጤት የሚገልጽ ሰርቴፊኬት የሚያቀርቡና ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና ህጎችን የሚያሟሉ መሆኑን በሚል የተቀመጡት መስፈርቶች በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዳይካተቱ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ መስፈርቶች እራሳቸውን በቻለ በሌሎች ሕጎች የሚሸፈኑ እንጂ በዚህ መመሪያ ውስጥ በመስፈርትነት ለማካተት የሕግ መሰረት ስለሌለው እንዳይካተት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 11)

5) **የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ ስለመመልመል**

በአዋጁ ከተሰጡ ስድስት ዓይነት የማበረታቻ ሥርዓቶች አንዱ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ነው(በአዋጁ አንቀጽ 3(1)(ረ)፣ 13 እና 14 ይመለከቷል)፡፡ የዚህ ሥርዓት ተጠቃሚ የሚሆኑ አምራቾችን ለመየለየ የሚያስችል መስፈርት በመመሪያ ተካቶ መውጣት እንዳለበት አዋጁ በግልጽ አመልክቶ ሳለ በነባሩ መመሪያ መስፈርቶቹ በግልጽ ሳይቀመጥ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ይህን ጉድለት ለመሙላት መስፈርቶቹን በግልጽ የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች እንዲያካትት ተደርጓል(አንቀጽ 13፣14ና 15)፡፡

6) **የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል ኃላፊነት፣**

- በነባሩ መመሪያ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው የሥራ ክፍል ማን እንደሆነ፣ ዝርዝር ተግባራቱ ምን እንደሆነ፣ የያዘ ድንጋጌ አልነበረም፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እነዚህ ጉዳዮች በዝርዝር እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡(አንቀጽ 13)

7) **የምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ**

- የማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው አስፈላጊ ከሆኑበት ምክንያቶች አንዱ ለተጠቃሚዎች ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ነባሩ መመሪያው ተጠቃሚዎች የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ካመለከቱ በኋላ የምስክር ወረቀቱን የሚያገኙበት የጊዜ ገደብ አልነበረም፡፡ ይህን በማረም በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው የምስክር ወረቀት ሊሰጥ የሚገባበትን የጊዜ ገደብ አስቀምጠዋል፡፡(አንቀጽ 16)

8) **የምስክር ወረቀት ስለማደስ**

- በነባሩ መመሪያ የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማሳደስ ተጠቃሚው ቀረጥና ታክስ መክፈሉ እና በጸደቀላቸው የግብዓት ጥመርታ ላይ ለውጥ አለማድረጋቸውን የሚያመለክት የማረጋገጫ ደብዳቤ ከጉምሩክ ኮሚሽን እንዲያቀርቡ በመስፈርትነት የተቀመጠውን በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው እንዳይካተት ተደርጓል፡፡ እንዳይካተት የተደረጉበት ምክንያት በሌሎች ሕጎች የተሸፈኑ ስለሆነ እና የዚህ መመሪያ መሠረት ከሆነው አዋጅ ቁጥር 768/1995 የተፈጻሚነት ወሰን ውጪ በመሆኑ ነው፡፡ (አንቀጽ 19)
- በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ላይ ከታደሰ የንግድ ፈቃድ በተጨማሪ ተጠቃሚው በቀዳሚው አመት ያስገባውን ግብዓት በአንድ አመት ውስጥ ካልተጠቀመ ደግሞ ለኮሚሽኑ የማራዘሚያ ጥያቄ አቅርቦ ማስፈቀድ እንዳለበት በአዋጁ የተቀመጠውን አስገዳጅ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ለምስክር ወረቀት እድሳት እንደመስፈርት እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 19)

9) የምስክር ወረቀት ስለሚታገድበት እና ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

- በነባሩ መመሪያ የምስክር ወረቀት ሊታደግ እና ሊሰረዝ እንደሚችል እና የሚታገድበትን እና የሚሰረዝበትን ምክንያቶች ምን እንደሆኑ አልደነገገም፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ይህን ጉድለት ለመሙላት የምስክር ወረቀት ሊታገድ እና ሊሰረዝ ስለሚችልበት ሁኔታ የሚያመለክት ድንጋጌ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 20 እና 21)

10)የአገልግሎት ክፍያ

- የአገልግሎት ክፍያ መጠንን የመወሰን ሥልጣን ያለው በገንዘብ ሚኒስቴር መመሪያ ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ነው፡፡ ነገር ግን በነባሩ መመሪያ የአገልግሎት ክፍያ መጠን ተቀምጠዋል፡፡ ሕጋዊ መሠረት የሌለው ድንጋጌ ስለሆነ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው የአገልግሎት ክፍያ መጠን እንዳይካተት ተደርጓል፡፡ ነገር ግን የአገልግት ክፍያ እንደሚኖር በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ተመላክቷል፡፡(አንቀጽ 22)

11) ቅሬታ ስለማቅረብ

- በነባሩ መመሪያ ባለጉዳዮች ያላቸው ቅሬታ የሚስተናገድበትን አግባብ የተመለከተ ድንጋጌ አልያዘም፡፡ በማሻሻያ ረቂቅ መመሪያው ይህን ክፍተት ለመሙላት አዲስ ድንጋጌ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡(አንቀጽ 23)